# ዐራት ትፍጽምት ያለው ግጥም
## ፬



ድብር ባለበት ቀን ጭጋግ በለበሰ
ያ ክፉ ጅብ መጣ እያነካከሰ
አህያየ ጠፍታ ስፈልጋት ውየ
ቤት ልመለስ ነበር ጠፍታ ትቅር ብየ
‘ግን ያ ክፉ ሽባ ያገኛት እንደሆን
ጸጸቱ አይወጣልኝ መቸውኑም ቢሆን…’
ብየ ተከትየው ዱር-ለዱር ስገዝ
ሜዳና፣ ተራራ፣ ሸለቆና፣ ወንዝ፣
ወጣሁኝ፣ ወረድኹኝ፣ ያንን ሁሉ በ’ግሬ
ሌ’ቱም ጨለመና ስኳትን አድሬ
ጥዋት ቤት ስገባ በድካም ሰክሬ
ያች ሓፍረተ-ቢሷ ቆማለች ከበሬ!
“ወየት አባሽ አደርሽ?” ብየ ተናድጄ
ዠለጥኳት በያዝኩት ዱላ በቀኝ እጄ
“ኦረ አንተው የት አደርክ?” ብላ ተገልብጣ
አሽቀነጠረችኝ ወደ ኋላ ረግጣ።
“ኦረ! እንዲህ ናትና…” ብየ ተነስቼ
ድብን ላ’ረጋት ስል ሽጉጤን አውጥቼ፣
“ተው እኮ ምን ነካህ፣ ጤናም አይደለህ?
ጅብዱ ሊባል ነው ወይ አህያህ ገድለህ?”



ብላ በመገረም ዓይኖቿን አፍጥጣ
ትጠይቀኝ ጀመር ደፋሯ፣ ዓይን አውጣ፤
“እስኪ ምን በደልኩህ በዚህ በማለዳ
“የምታወርድብኝ የዱላህን ናዳ?
“ቤቱን ዘግተህ ሄደህ፣ መግብያም አጥቼ
“ስጠብቅ አድሬ፣ ከውጭ ተጎልቼ
“የትም ስትሰክር፣ ስትዞር አድረህ
“ኦረ ለመሆኑ ምን ዓይነት ሰው ነህ?
“ምንም ሳትጠይቅ ጉዳይ አስለህ
“እንዲያው መማታቱ ማለዳ መጥተህ
“እንዲህ ያለ በደል ሰውም አይሰማህ።
“ጎረቤት ይፍረደው ዘመድ ይሁን ባዳ
“ምክንያትም ካለህ ዘርዝርና አስረዳ…”

“ዝም በዩ ለፍላፊቱ፣ ሰማሁልሽ በቃ
“ልደባልቅሽ ነው ካፈርና ጭቃ
“አንድም ቃል አይውጣሽ፣ አፍሽንም ዝጊው
“ፈጣሪን ከልብሽ ይቅርታ ጠይቂው።
“ጌታሽን በእርግጫ ከሆዱ መትተሽ
“ደግሞ መሞጣሞጥ፣ ፍጹም አልለቅሽ!
“እኔ ቆርጫለሁ፣ አልቀልሻልና
“ቶሎ ተዘጋጂ ንስሓ ግቢና…”
ብየ አቀባበልኩት፣ ሽጉጡም ጎረሰ
የመሞቻዋ ቀን ዕለቱ ደረሰ
ወስጄ ደገንኩት ከግንባሯ ላይ
አይገድለኝም ብላ ዓይን-ዓይኔን ስታይ
የመሞቻዋ ቀን በእርግጥ ደረሰ
ቃታውን ስስበው ግንባሯ ፈረሰ
ጥይቱ ገባና ወደ አንጎሏ ውስጥ
አጨማለቀልኝ አ'ርጎ ፍርጥርጥ።
ወድቃ፣ ተንፈራፍራ፣ ከእግሮቼ በታች
በቃት አህያየ ወድያውኑ ሞተች።



እስቲ ምን ይባላል እኔው ከምገድላት
ከዚያው ከዱር ጠፍታ ያ ጅብስ በበላት!
ዓርፌ፣ ተኝቼ ከአልጋየ ባደርኩኝ
ተራራ፣ ሸለቆ፣ ባልተንከራተትኩኝ!
ምንኛ ዕድለኛ፣ ጤና ሰው በሆንኩኝ!
ሌቱን ሙሉ ስዞር ድካሜ እንዲያ በዝቶ
እግሬ፣ አውራ ጣቴ ዕንቅፋት ተመትቶ
ማለዳም በእርግጫ ሆዴ ተነርቶ
በዚያች በገጣባ፣ ጀርባዋ ድሪቶ
ምላሷ ሾለብኝ ወጣ ተዘርግቶ
በእርሷስ የተነሳ አልታደልኩም ከቶ!
አሁን ከበራፌ ጥንቧ ተጎልቶ
ቶሎ ካልተጣለ ጫካ ተጎትቶ
ጉዴ ሊፈላ ነው ሰፈር ሁሉ ገምቶ…
ይህ የመሰለ ጉድ እስኪ ከየት መጣ?
አያድርስባችሁ እንዲህ ያለ ጣጣ
መዓት ነው ዘንድሮ፣ አረ ጉዴ ወጣ!



ገ/ኢ. ጐርፉ።